56. እግዚአብሔር አዳምን እንድትረዳ ማንን ፈጠረ?

ሀ- የመጀመሪያዋን ሴት ሔዋንን ፈጠረ።

57. እግዚአብሔር ሔዋንን ለምን ፈጠረ?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን እጅግ ስለሚወደው ነው።

ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳም ብቻውን እንዳይሆን ስለፈለገ ነው።

ሐ- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ልጆች እንዲወልዱ ስለ ፈለገ።

58. በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት ሲኖሩ እንዴት ነበሩ?

ሀ- በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት ሲኖሩ እጅግ በጣም ደስተኞች ነበሩ።



## ትምህርት 10

1. በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ የሆነው መልእክት የማን መልእክት ነው?

ሀ- የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

2. የእግዚአብሔር መልእክት በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ መልእክት የሆነው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።

ለ- ሁሉም ሰው ዋሽቶአል።

ሐ- ሁልጊዜ እውነትን የሚናገር እግዚአብሔር ብቻ ነው።

3. ከመጀመሪያ በፊት ብቻውን ይኖር የነበረው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ነው።

4. እግዚአብሔር መኖር የጀመረው መቼ ነው?

ሀ- እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም።

5. እግዚአብሔርን የፈጠረው ይኖር ይሆን?

ሀ- የለም እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።

6. እግዚአብሔርን የፈጠረው ራሱ እግዚአብሔር ይሆን?

ሀ- አይደለም እግዚአብሔር አልተፈጠረም አልተወለደም።

ሐ- እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።

7. እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበር?

ሀ- አልነበረም እግዚአብሔር ሁልጊዜ ነበር።

8. እግዚአብሔር ይለወጣል?

ሀ- በፍጹም።

ለ- እግዚአብሔር ፈጽሞ አይለወጥም።

9. እግዚአብሔር ይሞታል?

ሀ- በፍጹም።

ለ- እግዚአብሔር አይሞትም።

10. እግዚአብሔር እንደ ሰው ሥጋና አጥንት አለው?

ሀ- የለውም።

ለ- እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

11. ሰዎች ለመኖር ምግብና ውሃ ያስፈልጋቸዋል እግዚአብሔር ለመኖር የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ለ- እግዚአብሔር ለመኖር ምንም አያስፈልገውም።

12. ታዲያ እግዚአብሔር የሚኖረው እንዴት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ነው።

13. እግዚአብሔር የት ነው ያለው?

ሀ- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ አለ።

14. ስንት እግዚአብሔር አለ?

ሀ- አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ያለው።

15. አንድ እግዚአብሔር የሆኑት ሦስቱ አካላት እነማን ናቸው?

ሀ- እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።



49. እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረ በኋላ ምንን እንዲቆጣጠር አደረገው?

ሀ- እግዚአብሔር አዳም መላውን አለምና በውስጡ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲቆጣጠር አደረገው።

50. እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ የት አስቀመጠው?

ሀ- በዔድን ገነት።

51. በዔድን ገነት መካከል እግዚአብሔር የተከለው የመጀመሪያው ዛፍ ምን ይባል ነበር?

ሀ- የሕይወት ዛፍ።

52. እግዚአብሔር በዔድን ገነት መካከል የሕይወትን ዛፍ የተከለው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አዳም ከዛፉ በልቶ ለዘላለም እንዲኖር ፈልጎ ነበር።

53. እግዚአብሔር አዳም ከፍሬው እንዳይበላ ያዘዘው ዛፍ ምን ይባላል?

ሀ- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችል የዕውቀት ዛፍ።

54. አዳም መልካምና ክፉን መለየት ከሚያስችለው የዕውቀት ዛፍ ከበላ ምን ይደርስበታል?

ሀ- አዳም ይሞታል።

55. ሞት ምንድን ነው?

ሀ- የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር መለየት።

ለ- የነፍስ ከሥጋ መለየት።

ሐ- ተለይቶ በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

41. ሰይጣን ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ- ሰይጣን ማለት «ጠላት» ማለት ነው።

42. ሰይጣንን የተከተሉት መላእክት አዲሱ ስማቸው ማን ነው?

ሀ- አጋንንት።

43. እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ያዘጋጀላቸው የቅጣት ቦታ ምን ይባላል?

ሀ- ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ይባላል።

44. ሰይጣንና አጋንንቱ የሚቃወሙት ማንን ነው?

ሀ- እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሥራ ይቃወማሉ።

45. እግዚአብሔር ምድርን ካዘጋጀ በኋላ ማንን ፈጠረ?

ሀ- የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ፈጠረ።

46. እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን የተለያዩ አድርጎ የፈጠረው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው በአምሳሉ ነው።

47. «እግዚአብሔር ሰዎችን በአምሳሉ ፈጠረ» ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን እንዲያውቁት አእምሮ ሰጣቸው፤

ለ- ሰዎች እርሱን እንዲወዱት ስሜትን ሰጣቸው፤

ሐ- ሰዎች ለእርሱ እንዲታዘዙ ፈቃድን ሰጣቸው ማለት ነው።

48. እግዚአብሔር ሰዎችን መልካም ወይስ ክፉ አድርጎ ነው የፈጠራቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠራቸው መልካም ብቻ አድርጎ ነው።



16. ሰማያትንና ምድርን ማን ፈጠራቸው?

ሀ- እግዚአብሔር።

17. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከምን ፈጠረ?

ሀ- እግዚአብሔር ምንም ነገር አልተጠቀመም።

ለ- እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው ከምንም ነበር።

18. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት ነበር የፈጠረው?

ሀ- በመናገር ብቻ ነበር።

19. እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ለመፍጠር የቻለው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ በመሆኑ።

ለ- የእግዚአብሔር ኃይል ማብቂያ የሌለው በመሆኑ።

ሐ- እግዚአብሔር የማይችለው ምንም ነገር የለም።

20. እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን መፍጠርን እንዴት አወቀ?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል።

ለ- የእግዚአብሔር ጥበብ ማብቂያ የለውም።

ሐ- እግዚአብሔር የማያውቀው ምንም ነገር የለም።

21. እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ምን አለ?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉም ነገር «መልካም ነው» አለ።

22. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ፍጹም አድርጎ ሊፈጥራቸው የቻለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

23. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የፈጠረው ለማን ነው?

ሀ- ለሰዎች ነው።

24. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለሰው የፈጠረው ለምንድን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም እርሱ እኛን በጣም ስለሚወደን ነው።

25. እግዚአብሔር የሁሉም ነገሮች ትክክለኛ ባለቤት የሆነው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ስለሆነ ነው።

26. እንድንታዘዝለት እግዚአብሔር ባለመብት የሆነው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለፈጠረንና ሕይወትንም ስለሰጠን ነው።

27. መላእክት ሁሉ ከየት መጡ?

ሀ- እግዚአብሔር ፈጠራቸው።

28. እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው ሥጋና አጥንት ሰጥቷቸው ነውን?

ሀ- አይደለም።

ለ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መናፍስት አድርጎ ነው።

29. እግዚአብሔር መላእክቱን የፈጠራቸው ከፊሉን መልካም፥ ከፊሉን ደግሞ ክፉ አድርጎ ነው?

ሀ- አይደለም።

ለ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መልካም ብቻ አድርጎ ነው።

30. እግዚአብሔር መላእክቱን የፈጠራቸው ርዳታ ፈልጎ ነውን?

ሀ- አይደለም።

ለ- እግዚአብሔር ርዳታ አይፈልግም።

31. ታዲያ እግዚአብሔር መላእክትን ለምን ፈጠራቸው?

ሀ- ስለሚወዳቸው ነው።



32. በመጀመሪያ ሁሉም መላእክት የት ነበሩ?

ለ- ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ ሰማይ ነበሩ።

33. መላእክት በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ መገኘት ይችላሉ?

ሀ- አይችሉም።

ለ- በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ መገኘት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

34. እግዚብሔር ጠቢብና ውብ አድርጎ የፈጠረው መልአክ ማን ይባል ነበር?

ሀ- ሉሲፈር ይባል ነበር።

35. አንድ ቀን ሉሲፈር ምን ሆነ?

ሀ- ሉሲፈር የራሱን ጥበብና ውበት ተመለከቶ ታበየ።

36. ሉሲፈር ምን ለማድረግ ነበር ያቀደው?

ሀ- እግዚአብሔርን ከዙፋኑ ለማውረድ ነበር።

37. ሉሲፈር ከዙፋኑ እንዲያወርደው እግዚአብሔር ፈቀደለት?

ሀ- አልፈቀደለትም።

38. እግዚአብሔር በሉሲፈር ላይ እጅግ ስለተቆጣ ምን አደረገበት?

ሀ- እግዚአብሔር ሉሲፈርን ከመንግሥተ ሰማይ አስወጣው።

39. እግዚአብሔር ሰይጣንን በተከተሉት መላእክት ከተቆጣ በኋላ ምን አደረገባቸው?

ሀ- እግዚአብሔር እነርሱንም ከሰማይ ወደ ምድር ወረወራቸው።

40. የሉሲፈር አዲሱ ስም ማን ነው?

ሀ- ሰይጣን ነው።